# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል

አዘጋጆች

ጀማል ሁሴን
ምኒሊክ አዲሱ
ሥራዉ መካሻ

ገምጋሚዎች

ሙስጠፋ ከድር
ሮዳስ ድሪባ
ገስጥ አሰፋ

ግራፊክስ ዲዛይን

ግርማ ዳርጌ
ኃ/ጊዮርጊስ ተመስገን

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን።


## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል።

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# ምዕራፍ አንድ

## ቁጥሮች እስከ 20 (20 ክፍለ ጊዜያት)

### መግቢያ

ተማሪዎች በቀጥታ መቁጠር ከመጀመራቸው በፊት አስቀድሞ ነገሮችን በተለያየ መስፈርት ለምሳሌ በቅርፅ ፤በመልክ ወዘተ የመመደብ ልምምድ ቢያደርጉ የተሻለ ነው፡፡ ለምሳሌ በሁለት መጠኖች መካከል ያለውን ዝምድና በማወዳደር ብዛታቸውን ማወቅ መቻል አለባቸው፡፡ በዚህ ምእራፍ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እንዲማሩ በስድስት ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ ተማሪዎቹ ቅድመ መደበኛ ትምህርት የተማሩ ወይም ያልተማሩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ለዚህ ቅድሚያ ሁኔታቸው ተገቢውን ግምት በመስጠት ትምህርቱን ማቅረብ ይጠቅማል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በስብስብ ውስጥ ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ፡፡
- እስከ 20 ያሉትን የመቁጠሪያ ቁጥሮች ያነባሉ፤ ይፅፋሉ፡፡
- የቁጥሮችን ትርጉም ይረዳሉ፡፡
- ቆጠራን ከቁስ ቁጥር ጋር ያገናኛሉ፡፡

**ምዕራፉን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

በአካባቢ በቀላሉ የሚገኙና ለመቁጠር አመች የሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶች

**ለምሳሌ፡-**

- ዶሚኖዎች፤ ቆርኪዎች፤ስዕላዊ መግለጫዎች
- አባካስ
- በወረቀት የታተሙ ቁጥሮች
- ፍላሽ ካርዶች የመሳሰሉት፡፡

## 1.1 ከ አንድ እስከ አምስት መቁጠር (2 ክፍለ ጊዜያት)

### 1.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡

- ቁሶችን በስብስብ መቁጠር፡፡

### 1.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎች ከ1 አስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን አሁን በትምህርት መልክ ሳይሆን በመቁጠር ደረጃ ከህይወታቸው ገጠመኞች አንዱ መሆን ያለፈበት ሊሆን ይችላል፡፡በዚህ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች በተለይም ለህጻናት ጨዋታ የህይወታቸው አካል መሆኑ አያከራክርም ፡፡ ለዚህም የህጻናት ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ ግምት በመስጠት እነዚህ ተማሪዎች ሂሳብን እጅግ ተግባራዊ በሆነ መንገድ በራሳቸው በተማሪዎቹ ተሳትፎ መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ልጆች የተለያየ የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ማለትም በመስማት፣በመዳሰስ እና በተግባር ስራ በመሳተፍ የበለጠ እንደሚማሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም ላይ በመስራት ተማሪዎች የቁጥሮቹ ትርጉምና ጽንሰ ሀሳቦችን በነባራዊ ተጨባጭ ነገሮችና ምስሎችጋር በተዛመደ መልኩ ማጎልበት እነደሚችሉ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ቁጥሮች እንደዚሁ ረቂቅ ጽንሰ ሀሳቦች ብቻ ሳይሆኑ ነባራዊ የህይወት አካል እንደሆኑ ለመረዳት ያግዛቸዋል፡፡ የተጻፉ አሀዞች የነባራዊ ነገር መግለጫ ናቸው፡፡ ይህንንም ተማሪዎች በሂደት መረዳት እንዲችሉ ለማመቻቸት ያግዙ ዘንድ የሚከተሉትን ምሳሌ ዓይነቶች መጠቀም ይቻላል

**ምሳሌ** ፡- ውሻ አራት እግር አለው

- እኔ አንድ እስክርቢቶ አለኝ፡፡
- እኔ ሁለት እግር እና ሁለት እጅ አሉኝ፡፡
- አንድ ወንድም እና አንድ እህት አሉኝ፡፡

የቁጥሮችን ጽንሰ ሃሳብ ለማስረዳት መምህሩ/ሯ ብቻ በቁሳቁስ ወይም በምስሎች(ስእሎች) አሃዞችን ማሳየትና ተማሪዎች ደግሞ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሥእሎች በመቁጠር መለያየታቸው ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ከላይ ለማስታወስ እንደተሞከረው የቁጥሮችን ጽንሰ ሀሳብ ለማጎልበት ተማሪዎች እራሳቸውን ቁሳቁስን በመጠቀም ወይም በመያዝ በጋራ እየተወያዩ በኋላም እራሳቸውን ችለው ለየብቻቸው መቁጠርና ከአሀዞቹ ጋር በማዛመድ መመራመር እንዲችሉ ማገዝና ለዚህም ተግባር በተቻለ አቅም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ ቀለል ባሉ የቁጥር መዝሙሮች ቢደገፍ አግባብነት እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡

- እስከ አምስት ያሉ ቁሶችን በማቅረብ ቁሱን በማሳየት እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የራሳቸውን እና የጓደኞቻቸውን ጫማዎች 1፣2 1፣2 እያሉ ይቁጠሩ፡፡
- ተማሪዎች ጣቶቻቸውን እንደ መቁጠሪያ በመጠቀም እያንዳንዱን ጣት ጋር በማዛመድ ይቁጠሩ ፡፡
- ተማሪዎች የቁጥር መዝሙር ይዘምሩ፡፡

### 1.1.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር

- ሕጻናትን ስለ አሳዩት ባህሪይ ለውጥና ክህሎት ለማወቅ በየግዜው ክትትልና ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋል። **የግምገማውም አላማ**

1. ተማሪው/ዋ ተፈላጊውን ክህሎት እውቀትና ችሎታ ማግኘቱን ወይም አለማግኘቱን/አለማግኘቷን ለመለየት ሲሆን ካላገኘ /ች ተጨማሪ ድጋፍና እርዳታ የሚያገኝበት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከቀሪዎች ጓደኞቹ/ቿ ጋር መራመድ እንዲችል/ትችል መረዳት ነው።

2. ሌላው አላማ ተማሪዋ/ው ያለውን ውስጣዊ እውቀትና ዝንባሌ ለመረዳት ይህንን እውቀት ችሎታና ዝንባሌ የበለጠ የሚያጎለብትበትን ምቹ ሁኔታ ቀስ በቀስ ለመፍጠርና ለማበረታታት ነው። ስለሆነም ተማሪዎች አንድ በአንድ ከ1 አስከ 5 መቁጠር መቻላቸውን ያረጋግጡ። በተጨማሪም ተማሪዎችን እንደሚከተለው ይመዝኑቸው።

- ➢ ከአንድ በመጀመር መቁጠር መቻላቸውን መጠየቅ አንድ ለአንድ ቁጥር ማንበብ ተክነዋል?
- ➢ ከአንድ በመጀመር በሃሳብ መቁጠር ይችላሉ?
- ➢ ተማሪዎችን ይመልከቷቸው ፤በቃል ይጠይቋቸው እና መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ።
- ➢ የተማሪዎቹ መቆጣጠሪያ ላይ ምልክት ያድርጉ።

## 1.2 ከስድስት እስከ ዘጠኝ መቁጠር (2 ክፍለ ግዜያት)

### 1.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- በጥምር ስብስብ መቁጠር።
- ስብስብ ቁሶችን ከቁጥራቸው ጋር ማዛመድ።
- እስከ 9 ያሉ ቁሶችን ብዛት ማስታዎስ።
  ለምሳሌ እንደ ነጥቦች ዓይነት
- የቁሶችን ብዛት በፍጥነት መጥራት።
- ከ9 በመነሳት ቁሶችን እየቀነሱ ወደ ኋላ መቁጠር።

- ከ1 የተለዩ ቁጥሮችን ወደፊት ከቁሶች ጋር መቁጠር፡፡

### 1.2.2 'ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም_በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴ እና ተግባራት

- 1 እስከ 5 ያሉትን ቁጥሮች ለማስተዋወቅ የተጠቀምንባቸው ዘዴዎች ስራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡
- የተለያዩ ቁሶችን እንደ ዶሚኖ ያሉ በላያቸው ላይ ምልክት ያለባቸውን በማቅረብ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን ሳይቆጥሩ ቁጥሮቹን ይለዩ፡፡
- ተማሪዎች ከ10 ባነሰ በማንኛውም ቁጥር በመጀመር ይቁጠሩ፡፡ ለምሳሌ ከ 5 ቢጀምሩ 6 ፣ 7 ፣ 8 ፣ 9 እያሉ ይቁጠሩ፡፡
- በላያቸው ላይ መቁጠሪያ ያለባቸው ፍሬሞች ለተማሪዎች አቅርቡላቸውና ተማሪዎቹ ፍሬሙን እያዩ ይቁጠሩ፡፡
- ከ 9 ያነሱ የተለያዩ ቁሶችን ያቅርቡላቸው፡፡

  ለምሳሌ እንደ ጠርሙስ ክዳን አይነት፣ ተማሪዎቹ በሁለት በሁለት እና በሶስት በሶስት ይቁጠሩ ፣ ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት በመዝለል ይቁጠሩ፡፡
- ለተማሪዎች ሁለት የመቁጠሪያ ስብስቦች እያንዳንዳቸው ከ 9 ያነሱ ይስጧቸው፡፡ተማሪዎቹ በሁለቱ ስብስቦ ውስጥ ያሉትን ይቁጠሩ፡፡
- ተማሪዎች የዶሚኖውን ነጥቦች ወይም በወረቀት ላይ የታተሙትን ነጠብጣቦችን አንድ በአንድ ሳይቆጥሩ ቁጥሮችን የማዳበር ክህሎት ያዳብሩ፡፡
- እስከ 9 ያሉ ቁሶችን ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡ በቀላል አደራደር አስቀምጡላቸው ተማሪዎቹ የቁሶቹን ብዛት ይለዩ፡፡

### 1.2.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 9 ያሉ ማንኛውንም አይነት ቁጥሮች ማንበብ መቻላቸውን መጠየቅ እና ማረጋገጥ፡፡
- ከማንኛውም ከ10 ከሚያንሱ ቁጥር በመነሳት መቁጠር መቻላቸውን መጠየቅ፡፡
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ከ 9 ካነሱ ቁሶች ስብስብ ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

## 1.3 ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ (4 ክፍለ ጊዜያት)

### 1.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡

- ✓ **ቁጥሮችን በቃል መጥራት፡፡**
- ✓ በተሰጠው ቁጥር የቁስ ስብስብ መስራት፡፡

## 1.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴና ተግባራት

ተማሪዎች ከ1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን አሁን በትምህርት መልክ ሳይሆን በመቁጠር ደረጃ ከህይወታቸው ገጠመኞች አንዱ መሆን ያለፈበት ሊሆን ይችላል፡፡በዚህ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች በተለይም ለህጻናት ጨዋታ የህይወታቸው አካል መሆኑ አያከራክርም ፡፡ ለዚህም የህጻናት ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛ ግምት በመስጠት እነዚህ ተማሪዎች ሂሳብን እጅግ ተግባራዊ በሆነ መንገድ በራሳቸው በተማሪዎቹ ተሳትፎ መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ እዚህ ላይ ልጆች የተለያየ የስሜት ህዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ማለትም በመስማት፣በመዳሰስ እና በተግባር ስራ በመሳተፍ የበለጠ እንደሚማሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህም ላይ በመስራት ተማሪዎች የቁጥሮቹ ትርጉምና ጽንሰ ሀሳቦችን በነባራዊ ተጨባጭ ነገሮችና ምስሎችጋር በተዛመደ መልኩ ማጎልበት እነደሚችሉ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ቁጥሮች እንደዚሁ ረቂቅ ጽንሰ ሀሳቦች ብቻ ሳይሆኑ ነባራዊ የህይወት አካል እንደሆኑ ለመረዳት ያግዛቸዋል፡፡ የተጻፉ አሀዞች የነባራዊ ነገር መግለጫ ናቸው፡፡ ይህንንም ተማሪዎች በሂደት መረዳት እንዲችሉ ለማመቻቸት ያግዙ ዘንድ የሚከተሉትን ምሳሌ ዓይነቶች መጠቀም ይቻላል

**ምሳሌ** ፡- ውሻ አራት እግር አለው፡፡

- እኔ አንድ እስክርቢቶ አለኝ፡፡
- እኔ ሁለት እግር እና ሁለት እጅ አሉኝ፡፡
- አንድ ወንድም እና አንድ እህት አሉኝ፡፡

የቁጥሮችን ጽንሰ ሃሳብ ለማስረዳት መምህሩ/ሯ ብቻ በቁሳቁስ ወይም በምስሎች(ስእሎች) አሃዞችን ማሳየትና ተማሪዎች ደግሞ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሥእሎች በመቁጠር መለያየታቸው ብቻ በቂ አየሆንም፡፡_በመሆኑም ከላይ ለማስታወስ እንደተሞከረው የቁጥሮችን ጽንሰ ሀሳብ ለማጎልበት ተማሪዎች_እራሳቸውን ቁሳቁስን በመጠቀም ወይም በመያዝ በጋራ እየተወያዩ በኋላም እራሳቸውን ችለው ለየብቻቸው መቁጠርና ከአሀዞቹ ጋር በማዛመድ መመራመር እንዲችሉ ማገዝና ለዚህም ተግባር በተቻለ አቅም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ ቀለል ባሉ የቁጥር መዝሙሮች ቢደገፍ አግባብነት እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራዊ ያድርጉ፡፡

- እስከ አምስት ያሉ ቁሶችን በማቅረብ ቁሱን በማሳየት እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የራሳቸውን እና የጓደኞቻቸውን ጫማዎች 1፣2 1፣2 እያሉ ይቁጠሩ፡፡
- ተማሪዎች ጣቶቻቸውን እንደ መቁጠሪያ በመጠቀም እያንዳንዱን ጣት ጋር በማዛመድ ይቁጠሩ ፡፡
- ተማሪዎች የቁጥር መዝሙር ይዘምሩ፡፡

### 1.3.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር

ሕጻናትን ስለ አሳዩት ባህሪይ ለውጥና ክህሎት ለማወቅ በየግዜው ክትትልና ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ተግባር**

ለትምህርቱ መግቢያ ይሆናቸው ዘንድ ተግባር 1.1፣1.2፣1.3 ያሰሯቸው፡፡

የቡድን ስራ 1.1 እና 1.2 ያሰሯቸዉ፡፡

**የመልመጃ 1.1 መልሶች**

1. አንድ 1 ፤ ሁለት 2 ፤ ሶስት 3 ፤ አራት 4 ፤ አምስት 5
2. አምስት 5 ፤ አራት 4 ፤ ሁለት 2 ፣ ሶስት 3 ፤ አንድ 1
3. 2 4 ፤ 1 4 ፤ 4

### 1.4 ከ6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ (4 ክፍለ ግዜያት)

### 1.4.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡፡

- ✓ ስብስብ ቁሶችን ከቁጥራቸው ጋር ማዛመድ፡፡
- ✓ እስከ 9 ያሉ ቁሶችን ብዛት ማስታወስ፡፡
- ✓ የቁሶችን ብዛት በፍጥነት መጥራት፡

### 1.4.2' ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴ እና ተግባራት

- 1 አስከ 5 ያሉትን ቁጥሮች ለማስተዋወቅ የተጠቀምንባቸው ዘዴዎች ስራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡
- የተለያዩ ቁሶችን እንደ ዶሚኖ ያሉ በላያቸው ላይ ምልክት ያለባቸውን በማቅረብ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን ሳይቆጥሩ ቁጥሮቹን ይለዩ፡፡
- ተማሪዎች ከ10 ባነሰ በማንኛውም ቁጥር በመጀመር ይቁጠሩ፡፡ ለምሳሌ ከ 5 ቢጀምሩ 6 ፣ 7 ፣ 8 ፣ 9 እያሉ ይቁጠሩ፡፡
- በላያቸው ላይ መቁጠሪያ ያለባቸው ፍሬሞች ለተማሪዎች አቅርቡላቸውና ተማሪዎቹ ፍሬሙን እያዩ ይቁጠሩ፡፡
- ከ 9 ያነሱ የተለያዩ ቁሶችን ያቅርቡላቸው፡፡
  ለምሳሌ እንደ ጠርሙስ ክዳን አይነት፣ ተማሪዎቹ በሁለት በሁለት እና በሶስት በሶስት ይቁጠሩ ፣ ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት በመዝለል ይቁጠሩ፡፡
- ለተማሪዎች ሁለት የመቁጠሪያ ስብስቦች እያንዳንዳቸው ከ 9 ያነሱ ይስጧቸው፡፡ተማሪዎቹ በሁለቱ ስብስቦ ውስጥ ያሉትን ይቁጠሩ፡፡6
- ተማሪዎች የዶሚኖውን ነጥቦች ወይም በወረቀት ላይ የታተሙትን ነጠብጣቦችን አንድ በአንድ ሳይቆጥሩ ቁጥሮችን የማዳበር ክህሎት ያዳብሩ፡፡

- እስከ 9 ያሉ ቁሶችን ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡ በቀላል አደራደር አስቀምጡላቸው ተማሪዎቹ የቁሶቹን ብዛት ይለዩ፡፡

### 1.4.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- እስከ 9 ያሉ ማንኛውንም አይነት ቁጥሮች ማንበብ መቻላቸውን መጠየቅ እና ማረጋገጥ፡፡
- ከማንኛውም ከ10 ከሚያንሱ ቁጥር በመነሳት መቁጠር መቻላቸውን መጠየቅ፡፡
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ከ 9 ካነሱ ቁሶች ስብስብ ጋር ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

**የመልመጃ 1.2 መልሶች**

1. 6 ስድስት ፤ 7 ሰባት ፤ 8 ስምንት ፤ 9 ዘጠኝ
2. 6፤8 ፤ 8፤ 7 ፤8

## 1.5 ዜሮ ቁጥር (2 ክፍለ ግዜያት)

### 1.5.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- የዜሮን ትርጉም መረዳት፡፡
- ዜሮን ማንበብ እና መፃፍ፡፡
- ዜሮን በመጠቀም ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡

### 1.5.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ነጠብጣብ የሌለው ዶሚና በመጠቀም ተማሪዎች ዶሚኖው ላይ ነጠብጣብ አለመኖሩን እንዲረዱ መምራትና ዜሮን እንዲረዱ ማገዝ፡፡
- ተማሪዎቹ ከ 1 እስከ 10 ያሉ ነጥቦች የተሳሉበት እና ምንም ያልተሳሉበት ሰሌዳ ይስጧቸው ፡፡ ስለዚህ የዜሮ ጽንሰ አሳብን ‹‹ምንም ነጥብ የለም›› ‹‹ ምንም ቁስ የለም›› እና ‹‹ምንም›› ምንም በሚለው ሀሳብ ይመሰረታል፡፡
- ተማሪዎች የቁጥር መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፡፡

  ለምሳሌ፡‹‹ 0 እንደ እንቁላል ማነው የሚበላ ....... ››

### 1.5.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- ተማሪዎች ስለ ዜሮ  የተረዱትን እንዲገልጹ መጠየቅ፡፡
- ዜሮን  ደጋግመው  እንድሉ ማድረግ፡፡
- ተግባር 1.4 እና 1.5 ያሰሯቸው፡፡

## 1.6 ከ10 እስከ 20 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች (2 ክፍለ ግዜያት)

### 1.6.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ከአንድ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በፊደል መፃፍ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ፡፡

### 1.6.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ❖ የተለያዩ  መልመጃወችን ለተማሪዎች በመስጠት እስከ 20 ያሉ  ቁጥሮችን በማንሳት መቁጠር እንዲካኑ ማድረግ፡፡
- ❖ ተማሪዎች‹‹ በሁለት  ይበልጣል››‹‹በሁለት  ያንሳል›› የሚለውን ዝምድና እንዲረዱ ማድረግ ምሳሌ 8 ከ6 በሁለት ይበልጣል እና 8 ከ10 በሁለት ያንሳል፡፡
- ❖ የቁጥሮችን ስእሎች አቅርቡላቸው እና ተማሪዎች እያንዳንዱን የቁጥር አህዝ ያንብቡ፡፡
- ❖ ስለ መቀነስ የሚያወሱ መዝሙሮችን ማዘመር፡፡

  **ለምሳሌ** ‹‹አምስት ትናንሽ ዝንጀሮዎች አልጋ ላይ ዘለሉ›› ወይም‹‹ አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ ዘመሩ››  ወዘተ፡፡
- ❖ የራሳቸውንና የጓደኛቸውን ጣቶች በመጠቀም በ5 ይቁጠሩ፤ 5 ከራሳቸው አንድ እጅ፤ 10 ሁለተኛው እጅ  ፤15 ከጓደኛቸው አንድ እጅ እና 20 ከጓደኛቸው ሁለት እጅ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ቁጥሮችን በተመጣጣኝ ስዕሎች  ይወክሉ፡፡
- ❖ ተማሪዎች እንዲቆጥሩ መጠየቅ፡፡

  ለምሳሌ ከ 13 እስከ 16
- ❖ የሁለት ቁሶችን ስብስብ ለተማሪዎች መስጠት እና ተማሪዎቹ  በአንደኛው ስብስብ ውስጥ ያለውን ቁስ መጠን ይናገሩ እና በሌላኛው ስብስብ ውስጥ ያለውን  ቁስ ይቁጠሩ፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከተወሰነ ቁጥር  በፊት እና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች  እንድለዩ መርዳት አስር መቁጠሪያዎች ይስጧቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ወደፊት እና ወደኋላ ይቁጠሩ ፡፡
- ❖ ወደኋላ ለመቁጠር መቁጠሪያዎችን ይቀንሱ፡፡

- ❖ መቁጠርና መንቀሳቀስ፡ ተማሪዎች ቁጢጥ ካሉበት እየተነሱ ከ 1 አስከ 10 ይቁጠሩ ተመልሰው ቁጢጥ እያሉ ወደ ኋላ ይቁጠሩ፡፡
- ❖ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እንዲለዩ የተለያየ ተግባራት ይስጡዋቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎች ከ20 ባነሰ በማንኛውም ቁጥር በመጀመር መቁጠርን ይለማመዱ፡፡

1.6.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- ➢ ተማሪዎች ከአንድ የተወሰነ ቁጥር ተነስተው እስከ 20 እንድ እንዲቆጥሩ እና ወደ ኋላ እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው፡፡
- ➢ ተማሪዎቹ እየዘለሉ ሲቆጥሩ ያስተዋሏቸው እና የስህተት መጠናቸው መቀነሱን መከታተል፡፡
- ➢ እስከ 20 ያሉ ማንኛውም ዓይነት ቁጥሮች ያነባሉ፡፡
- ➢ ተማሪዎች ማንኛውም ከ 20 ከሚያንስ ቁጥር በመነሳት መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ➢ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ከ 20 ካነሱ ቁሶች ስብስብ ጋር ማዛመድ፡፡

1.7 ከ10 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ (4 ክፍለ ግዜያት)

1.7.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት በሁለት መቁጠር፡፡
- ጣቶችን በአምስት መቁጠር፡፡
- ቁጥሮችን በአምስት መቁጠር ፡፡
- ከ20 በመነሳት ወደኋላ መቁጠር፡፡
- ከማንኛውም ቁጥር በመነሳት እስከ 20 ወደፊት መቁጠር፡፡
- ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ‹‹ከፊት›› ከኋላ›› እና በመካከል በመጠቀም ማስቀመጥ፡፡

## 1.7.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የቁስ ስብስብ ለተማሪዎች መስጠት እና ተማሪዎቹ ቁሶችን በጥንድ በማንሳት ድምፃቸውን እያወጡ እንዲቆጥሩ ማድረግ ከ20 ያልበለጡ ሆነው 2 ፣ 4 ፣ 6 እያሉ ይቁጠሩ፡፡
- ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በጥንድ በጥንድ ይቁጠሩ፡፡
- አንድ ፣ ሁለት ፣ ሶስት.....ተብለው የተፃፉ ቁጥሮች ይስጧቸው ወይም በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው ተማሪዎቹ ማንበብና መፃፍ ይለማመዱ፡፡

## 1.7.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎቹ የቁጥሮችን አሃዝና የቁጥሮችን መጠን በትክክል ማዛመዳቸውን ይመልከቱ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች እንዲያነቡ መጠየቅ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

### የማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

1. ሀ. አስር ለ. ስምንት ሐ. አምስት መ. አስራሁለት ሠ.አስራ ሰባት
2. ሀ. 4 ለ. 11 ሐ. 18 መ. 19 ሠ. 0
3. ሀ. 4 7 8

   ለ. 0 3 6

   ሐ. 1 4 5

# ምዕራፍ 2

## 2. ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ (11 ክፍለ ግዜያት)

### መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ማወዳደር ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም ለመስራት የቁጥር መስመር መጠቀም እንችላለን። ከዚህም በተጨማሪ ቁጥሮችን በአስር በአስር መመደብን ያዉቃሉ።

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

❖ ሁለት ቁጥሮችን ያወዳድራሉ።

❖ ሶስት ቁጥሮችን ያወዳድራሉ።

❖ ከ 1- 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ።

❖ የ < ፣ = እና >ምልክቶችን ለይተው ያዉቃሉ።

### ምዕራፉን ለማስተማር የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች:

- በተማሪዎች የመኖሪያ አካባቢ በቀላሉ የሚገኙና ለመቁጠር የሚመቹ ቁሳቁሶች

ለምሳሌ:- ጠጠሮች፣ የዛፍ ፍሬዎች፤ ቆርኬዎች ….ወዘተ

- ዶሚኖዎች
- የክርቢት እንጨት እና የብር ማሰሪያ
- ቁጥር የታተመባቸው ወረቀቶች
- ስእላዊ መግለጫዎች

## 2.1 ሁለት ቁጥሮችን ማወዳደር (3 ክፍለ ግዜያት)

### 2.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

❖ ‹‹ከግራ›› እና ‹‹ ከቀኝ›› በማለት ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማስቀመጥ።

❖ የቁስ ስብስቦችን በቁጥራቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ።

❖ በሁለት ምድብ ያሉ ቁሶችን በቁጥራቸው መጠን ማወዳደር።

❖ ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማወዳደር።

### 2.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ተማሪዎች ዶሚኖዎችን ወይም ቁጥር የታተመባቸውን ወረቀቶች በቁጥራቸው ብዛት ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲደረደሩ ማድረግ፡፡
- የቁጥር መስመርን ጽንሰ ሀሳብ እንድረዱ ዘንግ እና ቁጥሮች የታተሙባቸው ወረቀቶች ለተማሪዎች በመስጠት እያጣበቁ የቁጥር መስመር እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡

### 2.1.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- ሁለት ቁጥር ሰጥቶ የትኛው እንደሚበልጥ መጠየቅ፡፡
- የተማሪዎች መቆጣጠሪያ ላይ ምልክት በማድረግ ተማሪዎች እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን እና አሀዛቸውን ማገናኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

ተግባር 2.1 ያሰሯቸው፡፡

**የመልመጃ 2.1 መልሶች**

( ተማሪዎች ቀጥሮችን ለማወዳደር የቁጥር መስመር ቢጠቀሙ የተሻለ ነው)

1. ለ. > (አስራ ስድስት ይበልጣል ከ አምስት)

   ሐ. = ( ስምንት እኩል ነው ከስምንት)

   መ. > ሠ. < ረ. =

2. ሀ. 2፣ 3፣ 7፣ 8፣ 10

   ለ. 0 ፣3፣ 4፣ 5፣ 8፣ 9

   ሐ. 0፣ 2፣ 3፣ 5 ፣ 7፣ 8

3. ሀ. 9 ፣ 8 ፣ 7 ፣ 5 ፣ 3 ፣ 2

   ለ. 10 ፣ 9 ፣ 8 ፣ 5 ፣ 4

   ሐ. 9 ፣ 8 ፣ 7 ፣ 5 ፣ 2

## 2.2 ሶስት ቁጥሮችን ማወዳደር (3 ክፍለ ግዜያት)

### 2.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ‹‹በፊት›› ‹‹በኂላ›› እና ‹‹ በመካከል›› በማለት ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማስቀመጥ፡፡
- የቁስ ስብስቦችን በቁጥራቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡
- በሶስት ምድብ ያሉ ቁሶችን በቁጥራቸው መጠን ማወዳደር፡፡

❖ ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማወዳደር፡፡

### 2.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ዶሚኖዎችን ወይም ቁጥር የታተመባቸውን ወረቀቶች በቁጥራቸው ብዛት ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲደረደሩ ማድረግ፡፡
- የቁጥር መስመርን ጽንሰ ሀሳብ እንድረዱ ዘንግ እና ቁጥሮች የታተሙባቸው ወረቀቶች በመስጠት እያጣበቁ የቁጥር መስመር እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡

### 2.2.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- ሁለት ቁጥር ሰቶ የትኛው እንደሚበልጥ መጠየቅ፡፡
- የተማሪዎች መቆጣጠሪያ ላይ ምልክት በማድረግ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እና አሀዛቸውን ማገናኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

### የመልመጃ 2.2 መልሶች

1. ሀ. <፣< ለ <፣< . ሐ =፣=

   መ. <፣< ሠ . >፣> ·ረ >፣ >

2 .

| ቁጥሮች | በፊት | በኋላ |
|---|---|---|
| 5 | 4 | 6 |
| 10 | 9 | 11 |
| 13 | 12 | 14 |
| 14 | 13 | 15 |
| 7 | 6 | 8 |

3. ሀ. 7 ለ. 7 ሐ. 10 መ. 0 ሠ.6
4. 8

## 2.3 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል (3 ክፍለ ግዜያት

### 2.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ❖ የቁጥሮችን ቀዳማይ እና ተከታይ መለየት፡፡
- ❖ የቁስ ስብስቦችን በቁጥራቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡
- ❖ ከ1 አስከ 20 ያሉ ቁጥሮቿን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፡፡

### 2.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማርማስተማር ዘዴዎች

- ➢ ተማሪዎች ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡
- ➢ ቁጥሮችን በቅደምተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ፡፡

### 2.3.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር

- ከ 20 የሚያንሱ ሁለት ቁጥሮችን ማወዳደር መቻላቸውን መጠየቅ እና ማረጋገጥ፡፡

ተግባር 2.2 ያሰሯቸው፡፡

የመልመጃ 2.3 መልሶች

1. ሀ. 14 ፣ 15 ፣ 16 ፣ 17 ፣ 18

   ለ. 11 ፣ 12 ፣ 18 ፣ 19

   ሐ. 13 ፣14 ፣16 ፣17 ፣19

   መ. 12 ፣ 13 ፣ 15 ፣17 ፣19

2. ሀ. 17 ለ. 17 ሐ. 20 መ. 10 ሠ.16

3. ሀ. 12 ፣14 ፣15

   ለ. 16 ፣18 ፣ 19

   ሐ. 13 ፣ 15 ፣ 16

   መ. 17 ፣ 19

## 2.4 ቁጥሮችን በ10 ቡድን መክፈል (2 ክፍለ ግዜያት)

### 2.4.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

- ➢ ቁሶችን በአስር እና በአምስት መመደብ፡፡
- ➢ በሙሉ ቁጥር ውስጥ ስንት አስሮች እና አንዶች እነዳሉ መናገር፡፡
- ➢ ሁለት የቁስ ስብስቦችን 10 እስኪሆኑ ድረስ ማጣመር፡፡

### 2.4.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማርማስተማር ዘዴዎች

- የቁስ ስብስቦችን በመስጠት ተማሪዎች በአስር በአስር ቡድን እንዲመሰርቱ ማድረግ።
- ከ 20 የማይበልጡ የቁስ ስብስቦችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በአምስት እና በአስር ቡድን እንዲመድቡ ማድረግ።
- ቢበዛ 2 ባለ አስር ፍሬሞችን በማዘጋጀት እና መቁጠሪያ በማድረግ በአምዶች በመደርደር አምዶቹን አምስቱ እንደ አንድ ወይም አስሩን እንደ አንድ እነዲቆጥሩ እና በ 5 እና በ 10 ምድብ መስራትን መለማመድ።

### 2.4.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር

- ተማሪዎቹ በጨዋታ መልክ በ10 እና በሌሎች ቁጥሮች ምድብ መስራታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር 2.3 ያሰሯቸው።

**የመልመጃ 2.4 መልሶች**

**ለ. 10 እና 3 ሐ. 10 እና 5 መ.10 እና 2**

**ማጠቃለያ መልመጃ መልስ**

1. ሀ. 4 ለ. 7 ሐ. 13 መ. 1 ሠ. 10
2. ሀ. < ለ. > ሐ. = መ. <
   ሠ. > ረ. = ሰ. < ሸ. >
3. ሀ. 7 ፣ 6 ፣5 ፣4 ፣2
   ለ. 13 ፣12 ፣11 ፣ 10 ፣9
   ሐ. 20 ፣ 19 ፣18 ፣17 ፣16 ፣15
   መ. 5 ፣4 ፣3 ፣2 ፣1 ፣0
   ሠ. 8 ፣7 ፣6 ፣5 ፣4 ፣3
4. ሀ. 2፣ 3 ፣4፣ 5፣ 6፣ 7
   ለ. 9 ፣ 10 ፣ 11፣ 12 ፣ 13
   ሐ. 0 ፣ 1 ፣ 2፣ 3 ፣ 4፣5
   መ. 15፣ 16፣ 17 ፣18 ፣19፣ 20
   ሠ. 0 ፣ 1 ፣ 2 ፣ 3፣ 4፣ 5፣6
   ረ. 3፣5፣ 6፣7፣8

# ምዕራፍ 3

## 3. መደመር (19 ክፍለ ግዜያት)

*መግቢያ*

የዚህ መዕራፍ ትምህርት የሚያተኩረው የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ተማሪዎች ከ1 እስከ 20 ባሉ ቁጥሮች መደመርን ይተዋወቃሉ፡፡ የመደመር ስሌት በቁጥሮች የሚከናወን ነው፡፡ ይህም ለምሳሌ ሁለት ቁጥሮችን የመደመርን ያህል ብዛትና የጋራ ባህሪ ያላቸውን ነገሮች አንድ ላይ በመቀላቀል ብዛታቸውን ከመግለጽ ጋር የቅርብ ዝምድና አለው ፡፡ይህንንም ለማጎልበት የቁጥር መስመር መጠቀም ፣ ቁሶችን በመደባለቅ እና ሌሎችንም ዘዴዎችበመጠቀም የመደመር ጽንስ ሀሳብን እናስተዋውቃለን፡፡

የምዕራፍ የመማር ወጤቶችተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኂላ፡

- የተለያየ ዘዴዎችን በመጠቀም ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡
- የመደመርን ሂሳባዊ ገለፃ ይረዳሉ፡፡

### ምዕራፉን ለማስተማር በዋናነት የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- በተማሪዎች የመኖርያ አካባቢ በቀላሉ የሚገኙና ለመቁጠር የሚመቹ ቁሳቁሶች ለምሳሌ፡-ጠጠሮች፣ የዛፍ ፍሬዎች፣ወዘተ
- ዶሚኖዎች
- አባከስ
- የክርቢት እንጨቶች ፣ ወዘተ

## 3.1 መደመርን በተረት (3 ክፍለ ግዜያት)

### 3.1.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡

- የሁለት ቁሶችን በስብስብ ማደባለቅ እና አብሮ መቁጠር፡፡
- ከ10 ከሚያንስ ቁጥር ላይ ቀንሶ ሌላኛውን ቁጥር 10 ማድረግ፡፡
- ቀላል የመደመር አረፍተ ነገሮችን መፍታት፡፡
- የ " = " እና " + " ምልክት መረዳት፡፡

### 3.1.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ❖ የመደመር አረፍተ ነገር ያለበትን ታሪክ ለተማሪዎች መንገር፡፡ ለምሳሌ እንደ " አንድ ብርቱካን በጠረቤዛ ላይ አለኝ ሁለት ብርትካኖች ብጨምር በአጠቃላይ ስንት ብርትካኖች ይኖሩኛል?" ወዘተ
- ❖ የመደመርን ጽንሰ ሀሳብ ለማስረዳት የተለያየ ሞዴሎችን መጠቀም፡፡
- ❖ ተጨማሪ የመደመር ታሪኮችን ለተማሪዎች መንገር ፡፡ እንደ የእኔ እጆች እና የጓደኛዬ እጆች ቢቀላቀሉ ስንት እጆች ይሆናሉ? ፣ጣቶችን እንደ መደመር አይነት በቃላት መደመር ወይም ማቀላቀልን እና መቁጠርን የመሳሰሉ ታሪኮችን መንገር፡፡
- ❖ ሁለት የቁስ ስብስቦችን ለተማሪዎች መስጠት ተማሪዎቹ እያንዳንዱን ስብስብ እንዲቆጥሩ ከዛም እንዲያቀላቅሉ እና ሁሉንም በአንድ ላይ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡

### 3.1.3 የመማርማስተማር ዘዴዎች የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት፡

- ❖ ለመደመር አላማ የተሰጣቸውን ታሪክ ተማሪዎቹ ተገንዝበውት እንደሆነ ማረጋገጥ፡፡ ለምሳሌ እናቴ ሶስት ብርቱካን አባቴ ሁለት ብርቱካን ቢሰጡኝ አጠቃላይ ስንት ብርቱካን አሉኝ?
- ❖ ሁለት ተመሳሳይ የቁስ ስብስብ መስጠት እና እያንዳንዳቸው ምን ያህል እንደሆኑ መጠየቅ ፡፡ ሲደባለቁ ምን ያህል እንደሚሆኑ መጠየቅ፡፡ ወዘተ

ተግባር 3.1 ያሰሯቸው፡፡

የመልመጃ 3.1 መልሶች

ሀ. 7 ለ. 9 ሐ. 15

## 3.2 ወደፊት እየዘለሉ መቁጠር (2 ክፍለ ግዜያት)

### 3.2.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት፡

- ❖ የቁጥር መስመርን በመጠቀም ሁለት ቁጥሮችን መደመር፡፡

### 3.2.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር መስተማር ዘዴዎች

- ➢ መቁጠር ተማሪዎቹ ባለ 10 እና ባለ 12 መቁጠርያ እንዲኖራቸው እና በዴስካቸው ላይ በግራ እና በቀኝ ማድረግ፤ 4 እንዲቆጥሩ ማድረግ እና ወደግራ እጃቸው እንዲሸፍኑ ማድረግ እና ከ 4 በመነሳት 5፣6፣7፣ እያሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ➢ ተማሪዎቹ ከ1 በመነሳት በ 2፣ በ3 ወይም በ5 እየዘለሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ➢ ከ1 በተለየ መነሻ እየዘለሉ እንዲቆጥሩ ማበረታታት፡፡

### 3.2.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት፡

- ❖ ተማሪዎች የራሳቸውን ዘዴ በመጠቀም እንድደምሩ ማድረግ፡፡
- ❖ የተማሪዎቹን ማሳመኛ ምክንያቶች መረዳት ጥያቄዎችን እንዴት እንደተረዷቸው መጠየቅ፡፡
- ❖ ተማሪዎች እንዴት መቁጠር እንደሚቻል መጠየቅ፡፡
- ❖ ተማሪዎች የእኩል ይሆናል እና የመደመርን ምልክት መረዳታቸውን መጠየቅ፡፡

**የመልመጃ 3.2 መልሶች**

ሀ. 9፣ 15 ለ. 12 ሐ. 10

**3.3 5 ፣6፣7፣8፣9 እና 10ን መመስረት (2 ክፍለ ግዜ)**

### 3.3.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማርብቃት

- ❖ ሁለት ቁጥሮችን በማጣመር 5 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን መመስረት፡፡

### 3.3.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ❖ ተማሪዎች 5፣ 6፣7፣8፣9፣10 ቁጥሮችን ለመመስረት ሁለት ስብስቦችን በማጣመር የተለያዩ ሙከራዎችን በተጨባጭ ቁሶችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ ምሳሌ 9 ቁሶችን ለማግኘት 7 ቁሶችን እና 2 ቁሶችን መጠቀም
- ❖ ከላይ ባለው አሰራር መሰረት 6፣7፣8፣9 እና 10 የሚሰጡ ሂሳባዊ ገለጻዎች እንዲያዘጋጁ ማድረግ እና 10 ላይ የተለየ ትኩረት ማድረግ ለዚህም ስራ ዶሚኖዎችን መጠቀም፡፡

### 3.3.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባራት

- አንድ ቁጥርን በሁለት ቁጥሮች ጥምረት መግለጽ መቻላቸውን መጠየቅ እና ማረጋገጥ፡፡
- ተማሪዎችን 10 ን የሚመሰርቱ ቁጥሮችን መጠየቅ፡፡

ምሳሌ 1 እና 9 ፣ 2 እና 8 ፣ 3 እና 7 ፣ 4 እና 6

ተግባር 3.2 ያሰሯቸው፡፡

መልመጃ 3.3 መልሶች


6 እና 2
4 እና 4
1እና 7
8
8እና 0
5እና 3


6 እና 3
1 እና 8
2እና7
9
9እና 0
5እና 4

## 3.4 ቁጥሮችን መተንተን (3 ክፊለ ግዜያት)

### 3.4.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት፡

❖ አንድ የተሰጠ ቁጥርን በሁለት ቁጥሮች ድምር መግለጽ፡፡

### 3.4.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴ

➢ አንድ ቁጥር ለተማሪዎቹ በመስጠት በሁለት ቁጥሮች ድምር እንድገልጹ ማድረግ፡፡

ለምሳሌ 7=1+6 7=2+5 7=3+4

### 3.4.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር፡

➢ ተማሪዎች ከ1 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን አንዱን በመውሰድ መተንተን መቻላቸውን መጠየቅ፡፡

ተግባር 3.3 ያሰሯቸው፡፡

**የመልመጃ 3.4 መልሶች**

1. ሀ. 14 = 14+0 =13+1 = 12+2 = 11+3 = 10+4 = 9+5 = 8+6=7+7



ለ. 8=8+0=7+1=6+2=5+3=4+4




ሐ. 11=11+0=10+1=9+2=8+3=7+4=6+5



መ. 5=5+0= 4+1=3+2




2.ሀ.16=15+1=14+2=13+3=12+4=11+5=10+6= 9+7=8+8

ለ. 10 = 10+0=9+1=8+2=7+3=6+4=5+5

## 3.5 እጥፍ እና አቅራብ እጥፍ (2 ክፍለ ግዜያት)

### 3.5.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማርብቃቶች፡

- ሁለት ባለ አንድ አሀዝ እና አንድ አይነት ቁጥሮችን መደመር፡፡
- እጥፍና አቅራብ እጥፍን መፈለግ፡፡

### 3.5.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር መስተማር ዘዴዎች

- ቁሶችን እና ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹ እጥፍ ማድረግን ማለማመድ፡፡

  ለምሳሌ 2+2 = 4

  3+3=_______

  4+4= _______ ፣ ወዘተ

- ለተማሪዎች በጥፍና እጥፍ አቅራቢያ ባሉ ቁጥሮች መደመርን ያለማምዷቸው ለምሳሌ 4+5 ፣ 4+4 =8 እና አንድ ሲደመር ቅርብ ነው፡፡ ስለዚህ 4+5=9

### 3.5.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር፡

- ተማሪዎችን እጥፍና አቅራብ እጥፍ በመጠየቅ መቻላቸውን መገንዘብ፡፡

ምሳሌ የሶስት እጥፍ ስንት ነው?

የሶስት አቅራብ እጥፍ ስንት ነው? ወዘተ

ተግባር 3.4 ያሰሯቸው፡፡

### የመልመጃ 3.5 መልሶች

1. ሀ. 8 ለ. 12 ሐ. 14 መ. 4 ሠ. 5 ረ. 2

ሸ. 4 ቀ. 1 በ. 6 ተ. 9

2.

| ቁጥር | እጥፍ | አቅራብ |
|---|---|---|
| 3 | 6 | 7 |
| 5 | 10 | 11 |
| 7 | 14 | 15 |
| 9 | 18 | 19 |
| 8 | 16 | 17 |
| 6 | 12 | 13 |

## 3.6 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥሮችን መደመር (3 ክፍለ ግዜያት)

### 3.6.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት፡

- ሁለት ባለ አንድ አሀዝ ቁጥሮችን መደመር፡፡

### 3.6.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር መስተማር ዘዴዎች

- ተማሪዎች እየዘለሉ መቁጠር እና መደመር ያላቸውን ተዛምዶ ማሳየት፡፡ ለምሳሌ በ 2 እየዘለሉ መቁጠር እና 2 መደመር ተመሳሳይ ናቸው፡፡
- እነዚህን የሃሳብ ምልክቶች " +" እና " = " ለተማሪዎች በማስተዋወቅ እና ባለ አንድ አሀዝ ቁጥሮችን ደምሮ ማሳየት፡፡ ለምሳሌ 2+3 =5

### 3.6.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር፡

- ተማሪዎች ሁለት ባለ አንድ አሀዞችን መደመር መቻላቸውን መጠየቅ፡፡

ለምሳሌ 2+1=3 ፣ 2+2 = 4 ፣ 2+3 =5 ፣ 2+4 = 6 ፣ 7+8 =15... ወዘተ ተግባር 3.5 ያሰሯቸው፡፡

**የመልመጃ 3.6 መልሶች**

1. ሀ. 2 ለ. 9 ሐ. 8
   መ. 10 ሠ. 6 ረ. 10

2. ሀ. 4 ለ. 8 ሐ. 4 መ. 1
   ሠ. 1 ረ. 2 ሰ. 6
3. 2+4 = 6
4. 5+4 = 9

## 3.7 ባላ አንድ አሃዝን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮች ጋር መደመር (4 ክፍለ ግዜያት)

### 3.7.1 ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃት፡

- ባለአንድ እና ባለ ሁለት አሀዝ ቁጥሮችን መደመር፡፡

### 3.7.2 ንዑስ ርዕሱን ለማስተማር በመነሻነት ወይም በአማራጭነት የቀረቡ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ተማሪዎች የመደመር ምንነትን እንድረዱ የመደመር የእኩል አረፍተ ነገሮችን መስጠት፡፡ ( ምሳሌ ከሚከተሉት የእኩልነት ጥያቄዎች ውስጥ እውነት ወይም ሀሰት የሆነው የቱ ነው ?

6+1=6-1 7=8-1

5+2=2+5 4+1=5+2

- የድምር ውጤት እንዲፈልጉ ፕሮብሌሞችን መስጠት እንደ 3+4 = _____
  አንድ ያልታወቀ ቁጥር 3+ _____ =7
- ሁለቱም ያልታወቁ ቁጥሮች _____ + _____ =7

- የተለያዩ ሞዴሎች በማዘጋጀት ተማሪዎች የመደመር ትርጉም እንዲገባቸው ማድረግ፡፡
- ድምራቸው ከ 20 ያነሱ ባለሁለት እና አንድ አሃዝ ቁጥሮችን ለመደመር ሁለት ፍሬሞችን መጠቀም፡፡
- ተማሪዎች ቁልቁል የመደመር ስልት ወይም ሌላ ስልት ተጠቅመው እንዲደምሩ እና አልጎሪዝምን እንዲረዱ ተማሪዎችን ማዘጋጀት፡፡

❖ ድምራቸው ወይም ልዩነታቸው ከ20 ያልበለጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ (ለምሳሌ 5+2 ወይም 8-3 ስንት ነው)

### 3.7.3 የምዘና ስልቶችና ዝርዝር ተግባር:

➢ የተከታታይ የምዘና ስልት ተጠቅመን ተማሪዎች መቻል አለመቻላቸውን መገምገም፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው እያንዳንዳቸው ባለ አንድ እና ባለ ሁለት አሀዝ ቁጥሮችን መደመር መቻላቸው መገምገም፡፡

ተግባር 3.6 ያሰሯቸው፡፡

**መልመጃ 3.7 መልሶች**

1. ሀ. 12 ለ. 19 ሐ. 18

   መ. 20 ሠ. 16 ረ. 20

2. ሀ. 4 ለ. 16 ሐ. 4 መ.1 ሠ.1 ረ. 2 ሰ.4

**የማጠቃለያ መልመጃ መልስ**

1.ሀ



2. ሀ. 6 = 6+0=5+1=4+2=3+3




ለ 9=9+0=8+1 = 7+2=6+3=5+4



ሐ 3=3+0=2+1




መ.7=7+0=6+1=5+2=4+3



3. ሀ. 8 ለ. 10 ሐ. 8 መ. 3
ሠ. 6 ረ. 18 ሰ.20

4. ሀ. 5 ለ. 12 ሐ. 13 መ. 10 ሠ. 18

5.

| ቁጥር | እጥፍ | አቅራብ እጥፍ |
|---|---|---|
| 2 | 4 | 5 |
| 8 | 16 | 17 |
| 4 | 8 | 9 |
| 9 | 18 | 19 |
| 1 | 2 | 3 |

6. 10+5=15

7. 2+4= 6

8. 3+3=6

# ዋቢ መፅሐፍት

ሀሰን መሀመድ መሰረታዊ የሂሳብ አጋዥ መፅሐፍ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፊያ ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ አዲስ አበባ 2006 ዓ.ም.

ኤን ሲ አር ቲ  የተማሪዎች መማሪያ መፅሓፍ 2021/2022.

Cambridge Curriculum framework (2021)

Kipp-Nashville (2020); grade 1 math practices workbook; (United state)

Virginia Department of education (2018) Mathematics instructional plan grade 1 double and near-double.

Nied (2015) teacher manual Mathematics grade 1 (Namibia) ; w.site(htt.//www.nied.edu.na)

Aggarwal, J.C (2016), Principle, methods and techniques of teaching. Vikas publishing House pvt. Limited; New Delhi

# ሒሳብ 1ኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1: ቁጥሮች እስከ 20 (20 ክ/ጊዜያት)

የመማር ውጤቶች፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣

- በስብስብ ውስጥ ያሉ ቁሶችን ይቆጥራሉ
- እስከ 20 ባሉ በቁጥሮችና በቁሶች መሀከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ
- ቆጠራን ከ ቁስ ቁጥር ጋር ያገነኛሉ
-

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ቁጥሮችን በቃል መጥራት<br><br>• ቁሶችን በስብስብ መቁጠር<br><br>በተሰጠው ቁጥር የቁስ ስብስብ መስራት | 1.1. ከ1- 5 መቁጠር | •ተማሪዎች የቁጥር መዝሙር ይዘምሩ<br><br>•እስከ 5 ያሉ ቁሶችን በማቅረብ ተማሪዎች ቁሱን በማንሳት ይቁጠሩ፣<br>ተማሪዎ የራሳቸውን እና ጓደኞቻቸውን ጫማዎች 1፣2 1፣2 እያሉ ይቁጠሩ<br><br>•ሶስት ቁሶችን እንደ ባህላዊ ምድጃ በማስቀመጥ 1፣ 2፣3 እያሉ ይቁጠሩ<br><br>•ተማሪዎች ጣቶቻቸውን እንደ መቁጠሪያ በመጠቀም እያንዳንዱን ጣት ከቁጥር ጋር በማዛመድ ይቁጠሩ | • የተማሪዎቹ መቆጣጠሪያ ላይ ምልክት ያድርጉ<br>•ከ1 በመጀምር መቁጠር መቻላቸዉን መጠየቅ<br>•የአንድ ለ አንድ ቁጥርማንበብን ተክነዋል ?<br>•ከ1 በመጀመር በሃሳብ መቁጠር ይችላሉ?<br><br>• ተማሪዎቹን ይመልከቷቸው፡፡<br>በቃል ይጠይቋቸው እና መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ |

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • በጥምር ስብስብ መቁጠር<br>• ስብስብ ቁሶችን ከቁጥራቸው ጋር ማዛመድ<br>• እስከ 9 ያሉ ቁሶችን ብዛት ማስታወስ. ለምሳሌ እንደ ነጥቦች ዓይነት<br>• የቁሶችን ብዛት በፍጥነት መጥራት<br>• ከ 9 በመነሳት ቁሶችን እየቀነሱ ወደኋላ መቁጠር<br>• ከ1 የተለዩ ቁጥሮችን ወደፊት ከቁሶች ጋር መቁጠር | 1.2 ከ 6-9 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር | • የተለያዩ ቁሶችን እንደ ዶሚኖ ያሉ በላያቸው ላይ ምልክት ያለባቸውን በማቅረብ ተማሪዎቹ ምልክቶቹን ሳይቆጥሩ ቁጥሮቹን ይለዩ<br>• ተማሪዎች ከ10 ባነሰ በማንኛውም ቁጥር በመጀመር ይቁጠሩ( ለምሳሌ ከ 5 ቢጀምሩ 6፣7፣8፣9 እያሉ ይቁጠሩ)<br>• በላያቸው ላይ መቁጠሪያ ያላቸው ፍሬሞች ለተማሪዎች አቅርቡላቸው ተማሪዎቹ ፍሬሙን እያዩ ይቁጠሩ<br>• ከ9 ያነሱ የተለያዩ ቁሶችን ያቅርቡላቸው ለምሳሌ እንደጠርሙስ ክዳን አይነት፣ ተማሪዎቹ በሁለት በሁለት እና በሶስት በሶስት ይቁጠሩ፣ ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት በመዝለል ይቁጠሩ<br>• ለተማሪዎቹ ሁለት የመቁጠሪያ ስብስቦች እያንዳንዳቸው ከ9 ያነሱ ይስጧቸው። ተማሪዎቹ በሁለቱ ስብስቦ ውስጥ ያሉትን ይቁጠሩ<br>• ተማሪዎቹ የዶሚኖውን ነጥቦች ወይንም በወረቀት ላይ የታተሙትን ነጠብጣቦች አንድ በአንድ ሳይቆጥሩ ቁጥሮቹን የመለየት ክህሎት ያዳብሩ<br>• እስከ 9 ቁሶችን ለተማሪዎቹ ይስጧቸው። በቀላል አደራደር አስቀምጡላቸው፣ ተማሪዎቹ የቁሶቹን ብዛት ይለዩ<br> | •እስከ 9 ያሉ ማንኛውንም ዓይነት ቁጥሮችንእንዲያነቡ መጠየቅ<br>•ከማንኛውም ከ10 ከሚያንስ ቁጥር በመነሳት መቁጠር መቻላቸዉን መጠየቅ<br>•እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ከ 9 ካነሱ ቁሶች ስብስብ ጋር ያዛምዳሉ |
| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የዜሮን ትርጉም መረዳት | 1.3 ከ1-5 ያሉ ቁጥሮችን ማንባብና መጻፍ | • ነጠብጣብ የሌለዉ ዶሚኖው በመጠቀም ተማሪዎች ዶሚኖው ላይ ነጠብጣብ አለመኖሩን እንዲረዱ መምራት እና ዜሮን እንዲረዱ ማገዝ<br>• ለተማሪዎቹ ከ1 እስከ 10 ያሉ ነጥቦች የተሳሉበት እና ምንም ያልተሳለበት ሰሌዳ ይስጧቸው፡፡ ስለዚህ የዜሮ ጽንሰ ሃሳብን "ምንም ነጥብ የለም" "ምንም ቁስ የለም" እና "ምንም" በሚለው ሀሳብ ይመሰረታል | • ተማሪዎች ስለ ዜሮ የተረዱትን እንዲገልዑ መጠየቅ |
| • እስከ 20 ያሉ ቁሶችን በ 2 መቁጠር፣ 2፣4፣6 እና 10<br>• ጣቶችን በ 5 መቁጠር<br>• ቁጥሮችን በ 5 መቁጠር፣ 5፣10፣15፣20<br>• ከ 20 በመነሳት ወደኋላ መቁጠር<br>• ከማንኛዉም ቁጥር በመነሳትእስከ 20 ወደ ፊት መቁጠር | 1.4 ከ 6-9 ያለ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ | • ተለያዩ መልመጃዎችን ለተማሪዎች በመስጠት እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በማንሳት መቁጠር እንዲካኑ ማድረግ<br>• ተማሪዎች "በሁለት ይበልጣል" "በሁለት ያንሳል" የሚለዉን ዝምዲና እንዲረዱ ማድረግ ምሳሌ 8 6 ን በሁለት ይበልጣል እና 8 ከ 10 በሁለት ያንሳል<br><br>• የቁጥሮችን ስዕሎች አቅርቡላቸው እና ተማሪዎች እያንዳንዱን የቁጥር ሆሄ ያንብቡ<br>• ስለመቀነስ የሚያውሱ መዝሙሮችን ለምሳሌ "አምስት ትናንሽ ዝንጀሮዎች በአልጋ ላይ ይዘላሉ "ወይም " አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ" ይዘምሩ፡፡.<br>• የራሳቸውንና የጓደኛቸውን ጣቶች በመጠቀም በ5 ይቁጠሩ፡፡ 5 ከራሳቸው አንድ እጅ፣ 10 ከሁለተኛው እጅ ፣15 ከጓደኛቸው አንድ እጅ እና 20 ከጓደኛቸው ሁለት እጅ<br> | • ተማሪዎች ከአንድ የተወሰነ ቁጥር ተነስተው እስከ 20 እንዲቆጥሩ፣ እና ወደ ኋላ እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው<br>• ተማሪዎቹ እየዘለሉ ሲቆጥሩ ያስተውሏቸው እና የስህተት መጠናቸው መቀነሱን መከታተል<br>• •እስከ 20 ያሉ ማንኛውንም ዓይነት ቁጥሮች ያነባሉ<br>•<br>• •ከማንኛውም ከ20 ከሚያንስ ቁጥር በመነሳት መቁጠር መቻላቸዉን መጠየቅ<br>• •እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ከ20 ካነሱ ቁሶች ስብስብ ጋር ያዛምዳሉ |

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ “ከፊት” “ከኋላ” እና በመሃል በመጠቀም ማስቀመጥ | | • ተማሪዎች ቁጥሮችን በተመጣጣኝ ስዕሎች ይወክሉ<br>• ተማሪዎችን እንዲቆጥሩ መጠየቅ ለምሳሌ “ከ 13 እንከ 16 ”<br>• የሁለት ቁሶች ስብስብ ለተማሪዎች መስጠት እና ተማሪዎቹ በአንደኛው ስብስብ ውስጥ ያለውን ቁስ መጠን ይናገሩ እና በሌላኛው ስብስብ ውስጥ ያለውን ቁስ ይቁጠሩ<br>• ተማሪዎች ከተወሰነ ቁጥር በፊትና በኋላ ያሉትን ቁጥሮች እንዲወስኑ መርዳት<br>አስር መቁጠሪያዎች ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎቹ ወደፊትና ወደኋላ ይቁጠሩ፡፡ ወደኋላ ለመቁጠር መቁጠሪዎቹን ይቀንሱ፡፡<br>መቁጠርና መንቀሳቀስ፡ ተማሪዎች ቁጢጥ ካሉበት እየተነሱ ከ1 እስከ 10ይቁጠሩ ተመልሰው ቁጢጥ እያሉ ወደ ኋላ ይቁጠሩ<br>• ተማሪዎቹ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እንዲለዩ የተለያዩ ተግባራት ይስጧቸው፡፡.<br>• ተማሪዎቹ ከ 20 ባነሰ በማንኛውም ቁጥር በመጀመር መቁጠርን ይለማመዱ. | |
| •ከ1-20 በፊደል መጻፍ<br>• እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ | 1.5 ዜሮቁጥር | • የቁሶች ስብስብ ለተማሪዎች መስጠት እና ተማሪዎቹ ቁሶችን በጥንድ በማንሳት ድምጻቸውን እያወጡ እንዲቆጥሩ ማድረግ ከ20 ያልበለጡ ሆነው 2፣4፣6 እያሉ ይቁጠሩ<br>ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በጥንድ በጥንድ ይቁጠሩ.<br>• “አንድ፣ሁለት፣ ሶስት …” ተብለው የተጻፉ ቁጥሮች ይስጧቸው ወይም በሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው ተማሪዎቹ ማንበብ እና መጻፍ ይለማመዱ.<br> | •የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎቹ የቁጥሮችን አሃዝና የቁሶችን መጠን በትክክል ማዛመዳቸውን ይመልከቱ<br>• እስከ 20 ያሉ ማንኛዉንም ቁጥሮች እንዲያነቢ መጠየቅ<br>•እስከ 20 ያሉ ማንኛውንም ዓይነት ቁጥሮች ይጽፋሉ<br>. |

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • እስከ 20 ያሉ ቁሶችን ብዛት በቅደም ተከተል መረዳት<br>• በቤት ቁጥር ላይ ያሉትን የቁጠር ሆሄዎች ማንበብ<br>አንድ ለአንድ በማጋጠም ፕሮብሌሞችን መፍታት ተመጣጣኝ የሆኑ እስከ 20<br><br>• ቁሶች ከተቆጠሩ በኂላ በመጨረሻ ያለውን ቁጥር በመንገር የቁሶችን ብዛት መረዳት<br>• እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በተለያየ ነገር እንደ ሞዴል ስዕሎችና የቁጥር ገለጻ መወከል | 1.6 ከ10-20 ያለ መቁጠሪያ ቁጥሮች<br><br><br><br>1.7 ከ10 -20 ያለ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ | • ተማሪዎቹ ቁጥሮችን በተለያየ ውክልና እንዲገልጹ ይጠይቋው። (ጣታቸውን በመቁጠር፣ ስዕል በመሳል፣ ወይም በፊደል በመጻፍ ሊሆን ይችላል) ተማሪዎች ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው።.<br>• ተማሪዎች የተለያዩ ቁጥሮችን በተለያዩ ሞዴል እንዲወክሉ ያግዟቸው፣ በተለያየ አቀማመጥ መስመራዊ፣ (ቀጥ ያለ፣አግድም፣ ሰያፍ)፣ ድርድር(አራት መኣዘን፣ሦስት ማእዘንክብ፣ የተበታተነ፣ በዘፈቀደ የተቀመጠ) ማዘጋጀት<br><br>• 20 ያነሱ የተለያዩ ቁሶችን ያቅርቡላቸው ለማሳሌ እንደጠርሙስ ክዳን አይነት፣ ተማሪዎቹ በሁለት በሁለት እና በሶስት በሶስት ይቁጠሩ፣ ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት በመዝለል ይቁጠሩ<br>• የተለያየ መጠን ያላቸው የቁስ ስብስቦችን ያቅርቡላቸው አብሮም የተለያዩ ጥያቄዎች ያቅርቡላቸው “ማን ብዙ ይዟል?” “በቂ መጠን አለ?” “ ምን ያህል ናቸው?” ስለሆነም ተማሪዎች የቁጥርን ጽንሰ ሀሳብ ያዳብራሉ<br>• ተማሪዎች አንደኛ፣ሁለተኛ፣ ሦስተኛ... ወዘተ የሚሉ ትርጉሞችን እንዲረዱ የተለያዩ ሞዴሎችን መጠቀም ምሳሌ ደረጃ ወይም ሌላ አካላዊ ቅደም ተከተል<br>• ተማሪዎች እንደ 10ኛ፣9ኛ...2ኛ ፣1ኛ ያሉ ከላይ እስከ ታች ተራዎችን እንዲጠቀሙ መርዳት<br> | • ተማሪዎች የቁጥር ትርጉም መረዳታቸዉን መመልከት፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና የተለየያ ግምገማ ስልቶችን መጠቀም |

# ምዕራፍ 2: ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ *(11 ክ/ጊዜያት)*

## የመማር ውጤቶች: ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

- ሁለት ቁጥሮችን ማወዳደር ይችላሉ
- ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይችላሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • “በፊት” “በኋላ” እና በመካከል” በማት ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማስቀመጥ<br>• የቁስ ስብስቦችን በቁጥራቸው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ<br>• በሁለት ምድብ ያሉ ቁሶችን በቁጥራቸው መጠን ማወዳደር<br>• ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ ማወዳደር<br>• ቁሶችን በአስር እና በአምስት መቦደን<br>• ሁለት የቁስ ስብስቦችን 10 እስኪሆኑ ድረስ ማጣመር<br>• በሙሉ ቁጥር ውስጥ ስንት አስሮ እና አንዶች እንዳሉ መናገር<br>• የቁጥር ቤት ዋጋ ጽንሰ ሃብን ማዳበር | 2.1 ሁለት ቁጥሮችን ማወዳደርር<br>2.2 ሶስት ቁጥሮችን ማወዳደር<br>2.3 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ<br>2.4 ቁጥሮችን በ10 በ10 ቡድን መመደብ | • ዶሚኖዎችን ወይም ቁጥር የታተመባቸውን ወረቀቶች በቁጥራቸው ብዛት ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲደረድሩ ማድረግ<br>• የቁጥር መስመርን ጽንሰ ሃሳብ እንዲረዱ ዘንግ እና ቁጥሮች የታተሙባቸውን ወረቀቶች በመስጠት እያጣበቁ የቁጥር መስመር እንዲሰሩ ማድረግ.<br>• ተማሪዎች ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ እንያወዳድሩ ማድረግ<br>• የቁስ ስብስቦችን በመስጠት ተማሪዎች በአስር በአስር ቡድን እንዲመሰርቱ ማድረግ<br>• ቢበዛ 2 ባለ አስር ፍሬሞችን በማዘጋጀት እና መቁጠሪያ በማድረግ በአምዶች በመደርደር አምዶችን አምስቱን እንደ አንድ ወይም አስሩን እንደ አንድ እንዲቆጥሩ እና በ5 እና በ 10 ምድብ መስራትን ማለማመድ.<br>• ከ20 በማይበልጡ የቁስ ስብስቦች ውስጥ ስንት አስሮች እና ስንት አንዶች እንዳሉ ተማሪዎቹን መጠየቅ<br>• ከ20 የማበልጡ የቁስ ስብስቦችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በአምስት እና በአስር ቡድን እንዲሰሩ ማድረግ<br>• የክብሪት እንጨቶች እና ብር ማሰሪ ላስቲክ ለተማሪዎቹ በመስጠት እየቆጡ አስር ሲሞላ በላስቲክ እንዲያስሩ ማድረግ ከዛም የታሰሩትን እና የተረፉትን የክብሪት እንጨቶች ውክልና እንዲያገናዝቡ ማድረግ | የተማሪዎች መቆጣጠሪያ ላይ ምልክት በማድረግ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እና አሃዛቸውን ማገናኘት መቻላቸውን መገንዘብ<br>የቃል ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎቹ ቁሶቹን፣ ቁጥሮቹን እና የቁጥር አሃዞቹን ማዛመዳቸውን ማረጋገጥ<br>ተማሪዎች ሞዴሎችን በትክክል በመጠቀም ገለጻ እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ<br>ተማሪዎቹ በጨዋታ መልክ በ10 እና በሌሎች ቁጥሮች ምድብ መስራታቸውን ማረጋገጥ |

# ምዕራፍ 3: መደመር (19 ክፍለ ጊዜያት)

## የመማር ብቃቶች-ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኂላ

- የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ቁጥሮችን መደመር ይችላሉ
- የመደመርን ሂሳባዊ ገለጻ ይረዳሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የሁለት ቁሶችን ስብስብ ማደባለቅ እና አብሮ መቁጠር<br><br>• ከ10 ከሚያንስ ቁጠር ላይ ቀንሶ ሌላኛውን ቁጥር 10 ማድረግ<br><br>• እነዚህን ምልክቶች መረዳት “+” “=”. | 3.1 የመደመርን በተረት<br><br>3.2 ወደፊት እየዘለሉ መቁጠር | • የመደመር አረፍተ ነገር ያለበትን ታሪክ ለተማሪዎች መንገር እንደ” አንድ ብርቱካን በጠረጴዛ ላይ አለኝ ሁለት ብርቱካኖች ብጨመር በአጠቃላይ ስንት ብርቱካኖች ይኖሩኛል”<br>• የመደመርን ጽንሰ ሀሳብ ለማስረዳት የተለያዩ ሞዴሎችን መጠቀም<br>• ተጨማሪ የመደመር ታሪኮችን ለተማሪዎች መንገር። ጣቶችን እንደመደመር አይነት በቃላት መደመር ወይም ማቀላቀልን እና መቁጠርን የመሳሰሉ ታሪኮችን።<br>• ሁለት የቁስ ስብስቦችን ለተማሪዎች መስጠት ተማሪዎቹ አያንዳንዱን ስብስብ እንዲቆጥሩ ከዛም እንዲያቀላቅሉ እና ሁሉንም በአንድ ላይ እንዲቆጥሩ ማድረግ<br>• መቁጠር፡ ተማሪዎቹ ባለ 10 እና ባለ 12 መቁጠሪያ እንዲኖራቸው እና በዴስካቸው ላይ በግራ እና በቀኝ ማድረግ፤ 4 እንዲቆጥሩ ማድረግ እና ወደ ግራ እጃቸው ወስደው እንዲሸፍኑ ማድረግ እና ከአራት በመነሳት 5፣6፣7፣ እያሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ<br>• ተማሪወቹ ከ1 በመነሳት በ2፣3 ወይም በ5 እየዘለሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ.<br>ከ1 በተለየ መነሻ እየዘለሉ እንዲቆጥሩ ማበረታታት<br><br><br><br><br>• ተማሪዎች 5፣6፣7፣8፣9፣10 ቁጥሮችን ለመመስረት ሁለት ስብስቦችን በማጠመር የተለያዩ ሙከራዎችን በተጨባጥ ቁሶችን እንዲሰሩ ማድረግ ምሳሌ 9 ለማግኛት 7 እና 2 መጠቀም<br>  ◦ ከላይ ባለው አሰራር መሰረት 6፣7፣8፣9 እና 10 የሚሰጡ ሂሳባዊ ገለጻዎ እንዲያዘጋጁ ማድረግ እና 10 ላይ የተለየ ትኩረት ማድረግ | ለመደመር አላማ የተሰጣቸውን ታሪክ ተማሪቹ ተገንዝበውት እንደሆነ ማረጋገጥ<br><br>ተማሪዎቹ የራሳቸውን ዘዴ እንዲናገሩ ማድረግ<br><br>ድምራቸው ወይም ልዩነታቸው ከ20 ያልበለጡ ጥያቄዎችን መጠየቅ (ለምሳሌ 5 + 2 ወይም 8 — 3 ስንት ነው)<br><br>ተማሪዎቹን ማሳመኛ ምክንያቶች መረዳት ጥያቄዎቹን እንዴት ተረዳሃቸው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 3.3 5፣6፣7፣8፣9 እና 10 መመስረት | <br><br>• ተማሪዎቹ 5 የሚሰጥ የመደመር መግለጫ እንዲጽፉ ማድረግ ለምሳሌ 3+2 እና 2+3፡፡ ይህንን 5 እንዲሰጥ በማድረግ ሂሳባዊ ገለጻ እንዲጽፉ ማድረግ | እንዴት በመቁጠር እንደሚቻል ልትነግረኝ ትችላለህ<br>የተማሪዎቹን የመረዳት እና የመደመርን ምልክት የመገንዘብ ብቃታቸውን አረጋግጥ |

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር | 3.4 ቁጥሮችን መተንተን<br><br>3.5 እጥፍ እና አቻ እጥፍ<br><br>3.6 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥሮችን መደመር | • ቁሶችን እና ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ተማሪዎቹ እጥፍ ማድረግን ማለማመድ 2+2፤3+3<br>• ለተማሪዎቹ በእጥፍ እና እጥፍ አቅራቢያ ባሉ ቁጥሮች መደመርን ያለማምዷቸው፡፡ ለምሳሌ 4+5፤ ለ 4+4 = 8 አን ሲደመር 1 ቅርብ ነው ስለዚህ 4+5 =9<br>• ድምራቸው ከ10 የማይበልጡ ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ላይ መደመር<br>• ተማሪዎችን እየዘለሉ መቁጠር እና መደመር ያላቸውን ተዛምዶ ማሳየት ለምሳሌ በ2 እየዘለሉ መቁጠር እና 2 መደመር ተመሳሳይ ናቸው እነዚህን የሂሳብ ምልክቶች "+" እና “=” ለተማሪዎች ማስተዋወቅ እና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ደምሮ ማሳየት 2+3=5 | እንዴት በመቁጠር እንደሚቻል ልትነግረኝ ትችላለህ<br>የተማሪዎቹን የመረዳት እና የመደመርን ምልክት የመገንዘብ ብቃታቸውንአረጋግጥ |

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ባለ አንድ እና ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን ይደምራሉ. | 3.7ባለአንድ አሃዞችን ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮች ጋር መደመር | • ተማሪዎች የመደመር ምንነትን እንዲረዱ መደመር የእኩል ዐ.ነገሮችን መስጠት(ምሳሌ ፡ ከሚከተሉት የእኩልነት ጥያቄዎች ውስጥ እውነት ወይም ሀሰት የሆነው የቱ ነው ?<br>6 + 1 = 6 — 1፣7 = 8 — 1፣5 + 2 = 2 + 5፣<br>4 + 1 = 5 + 2)<br>• የድምር ውጤት እንዲፈልጉ ፕሮብሌሞችን መስጠት እንደ 3 + 4 = ---- አንድ ያልታወቀ ቁጥር፣ 3 + ----- = 7፣ ሁለቱም ያልታወቁ ------- + --------- = 7፣ የተለያዩ ሞዴሎችን በማዘጋጀት ተማሪዎች የመደመር ትርጉም እንዲገባቸው ማድረግ<br>• ድምራቸው ከ20 ያነሰ ባለ ሁለት እና ባለ አንድ አሃዝ ቁጥሮችን ለመደመር ሁለት ፍሬሞችን መጠቀም። በአስር ፍሬምና አንዳንዱን መቁጠር<br>• ተማሪዎች ቁልቁል የመደመር ስልት ወይም ሌላ ስልት ተጠቅመው እንዲደምሩ፣ አልጎሪዝም እንዲረዱ ተማሪዎን ማዘጋጀት | |

## ምዕራፍ 4 ፣መቀነስ (20 ክ/ጊዜያት)

### የምዕራፉ የመማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ምዕራፍ ትምህርት በኋላ

- የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ቁጥሮችን ይቀንሳሉ፡፡
- በመደመርና በመቀነስ መሀከል ያለዉን ዝምድናይረዳሉ፡፡

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • *ወደኋላ በ2 እናበ3 መቁጠር*<br><br>• *ትልቁ ባለአንድ ሆሄ ላይ ትንሹን ባለአንድ ሆሄ መቀነስ* | **ምእራፍ 4 መቀነስ**<br>4.1 ወደ ኋላ መቁጠር<br>4.2 መቀነስን በተረት<br>4.3 ቁጥሮችንመተንተን<br>4.4 ባለ አንድ አሃዝ ቁጥሮችን መቀነስ<br>4.5 ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን መቀነስ | • ከ 20 በመጀመር በ2፣በ3፣ወይም በ5 ወደኋላ ቁጥሮችን መቁጠር<br>• የመቀነስ ፕሮብሌሞችን ምሳሌዎችን መንገር "ሰላም 7 እምነበረዶች አሏት ጥቂቶችን በመደበቅ ለናንተ አራቱን አሰየቻችሁ. ሰላም ምን ያህል የማይታይ እምነበረድ አሏት<br>• የተለያዩ ቅርጾችን በመጠቀም ቁሶችን በቡድን በማድረግ የአባከስ ስእሎች ወይም በካርዶች በመጠቀም የመቀነስ ጽንሰ ሃሳቦችን ማሻሻል<br>• ተማሪዎቹ ወደ ኋላ መቁጠርን ከመቀነስ ጋረ እንዲያዛምዱ መርዳት ለምሳሌ ወደ ኋላ በሁለት በሁለት መቁጠር በ2 መቀነስ መሆኑን መረዳት<br>• ተማሪዎቹ መቀነስን እንዲረዱ የማይታወቀወ ቁጥር እስከ 20 በመደመርእንዲያገኙመርዳት<br>• ምሳሌ 10 — 8 የሚለዉን መልስ ለማግኘት ከ 8 ላይ ስንት ተደምሮ 10 የሚያመጣውን ቁጥር መፈለግ<br>• ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ለመቀነስ የቁጥር መስመርን መጠቀም<br>  • የቁጥር መስመርን መጠቀም<br>5 ላይ ስንት ስደመር 8 ይሰጣል ?<br>ወይም ከ 8 ላይ ስንት ቢቀነስ 5 እናገኛለን?<br>ምስሉን ይመልከቱ.<br><br><br><br> | • የመቀነስ አረፍተ ነገሮችን የያዙ ምሳሌዎችን በመንገር የተማሪዎቹን ምላሽ ማረጋጥ<br>• ተማሪዎች የራሳቸዉን ስነዘዴዎች እንዲጠቀሙ መጠየቅ<br>• መልሳቸዉ 20 የሆነ ወይም ከ20 ያነሰ (ለምሳሌ 8-3) የመሳሰሉ የተለያዩ አይነት የመቀነስ ጥያቄዎችን መጠየቅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • “-“ ይህን የመቀነስ ምልክት ማወቅ<br><br>• ከ20 ያነሱ ባለ ሁለት ሆሄ ከአንደኛው ላይ ለተላኛዉን መቀነስ<br>• በመደመር እና በመቀነስ መሀከል ያሉ ዝምድናዎችን መረዳት<br><br>• ድምራቸዉ ከ20 ያነሱ ባሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በመደመርና በመቀነስ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት | 4.6 በመደመር እና በመቀነስ መሀከል ያለዉ ዝምድና<br><br>4 .7 የቃላት ፕሮብሌሞች | “-“ ይህን የመቀነስ ምልክት ማስተዋወቅ እና ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄቁጥሮችን እንዲቀንሱ ማድረግ ምሳሌ 5-3=2<br><br>መቀነስ የመደመር ተቃራኒ መሆኑን ከስር መሰረቱ መንገር<br><br>(ለምሳል 6+7=13 ስለዚህ 13- 7= 6)<br>ከእዉነተኛ መረጃ<br>በመነሳት መረጃዎችን የምናገናኝበት ዘዴ ነዉ<br><br><br>2+3=5<br>3+2=5<br>5-3=2<br>5-2=3<br><br>• የመደመር እና የመቀነስ ዝመድናዎችን በቁጥር ቤተሰብማሳየት<br><br>• ተማሪዎቹ የስሌቶች ባህሪዎች የሆኑትን (የመደመር የቅይይር እና የተጣማጅነት ባህሪይ) እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በመደመርና መቀነስ ስነዘዴዎችን እንዲተገብሩ ማገዝ(ለነዚህ ባህሪያት ደንቦችን መጠቀም አይጠበቅባቸዉም)<br>• የቃላት ፕሮብሌሞችን የመፍታት ስነዘዴዎችንና መፍትሄዎችን ማግኛ ዘዴዎችን ማብራራት<br>• የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመግለጽ ሞዴሎችን መጠቀም<br>• እስከ 20 ባሉ ቁጥሮች መደመርና መቀነስን ማእከል ያደረገ ፕሮብሌሞችን መስራት ይህም ቁሶችን እንድ ላይ በመደመር፣ በማደባለቅ፣በማንሳት፣በማወዳር በተጨማሪም ቁሶችና ቁሶችን ምስሎችን ያልታወቁ ተለዋዋጮችን ለእኩልነት አረፍተነገሮች በመጠቀም ፕሮብሌሞችን እንዲዎክሉ ማድረግ | ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ ምላሽ ሲሰጡ<br>• ምክንያታቸዉን<br>• አገላለጻቸዉን<br>• ግንኙነቶችን<br>ለምሳሌ<br>ፕሮብሌሞችን እንዴት መፍታት ትችላለችሁ ቁጥሮችን እንዴት ወደፊት እንደምተቆጥሩ ልትነግሩኝ ትችላለችሁ በማለት በመጠየቅ መገምገ<br><br>ተማሪዎቹ ያሉብትን ደረጃ ለማወቅ ፈተናዎችን በመስጠት ምላሻቸዉን መገምገም |

## ምዕራፍ 5፣ቁጥሮች እስከ 100 (25 ክፍለጊዜያት)

### የመማር ዉጤቶች፣ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

- በተለያዩ ዘዴዎች ቁጥሮችን ይቆጥራሉ
- መጠኖችን እና አቀማመጦችን ያላቸዉን ዝምድናዎችን ይረዳሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የ10 ብዜቶችን መቁጠር | ምእራፍ 5፣እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች<br><br>5.1 በ 10 በ10 ብዜቶች | •የ10 ብዜቶችን በቃላቸዉ እንዲቆጥሩ መርዳት<br>•የ10 ብዜቶችን ጽንሰሃሳብ ለማስጨበጥ በ10 በ10 ፍሬሞችን መጠቀም<br><br>•ቁሶችን በ10 በ10 በማቧደን የ10 ብዜቶችን ለመቁጠር መጠቀም<br><br>•መቶኛዎችን የያዙ ቻርቶች መስራት እና የ10 ብዘየቶችን እንዲረዱና እንዲገነዘቡ ማድረግ | • ቁጥሮችን ሲቆጥሩ በትክክል መጥቀሳቸዉን መጻመጥ |
| • እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በቃል መቁጠር<br><br>• ከ21 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በሬደሎች እና በአሃዞች ማንበብና መጻፍ | 5.2 ቁጥሮችእስከ 100 | • መቶኛዎችን የያዙ ቻርቶች መስራት እና በአንዶች ነ በአስሮች እንዲያነቡ ማድረግ<br>• ከ20 የሚበልጡ ቁጥሮችን ጮክ ብለዉ እንዲናገሩ መንገር እና<br>• ቁጥሮችን ወደ 10 አጠጋግተዉ እንዲያስቀምጡ መርዳት(ከ29 ወደ 30 ፣ ከ39 ወደ 40 ወ.ዘ.ተ)<br>• 29ን በ4 የሚበልጥ ቁጥር የቱ ነው? 29፣30፣31፣32፣33 መልስ 33 ስለዚህ ተማሪዎች ከቁጥር ተነስተው መቁጠር እንዲችሉ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የቁስ መጠን እንዲረዱ የተለያዩ አቀራረብ ዘዴዎችን መጠቀም ምሳሌ 34 ፣ለማስረዳት ብሎኮች በምስል ፣ የቁጥር መስመር፣ ፍሬሞችን መጠቀም<br><br><br> | መቶኛዎችን የያዙ ቻርቶችን ማዘጋጀት እና ቁጥሮችን በትክክል መጻፋቸዉንና ማንበባቸዉን መከታታል እና ማረጋገጥ |

<table>
<tr><th>ብቃቶች</th><th>ርዕሶች</th><th>የመማር ማስተማር ስልቶች</th><th>ምዘና</th></tr>
<tr>
<td><ul><li>እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማወዳደር የቁጥሮችን ቅደም ተከተል ለመለየት የቁጥር ደረጃን መጠቀምስለ ቁጥር ያላቸዉን የዉስጥ ሃሳባቸዉን እና እዉቀታቸዉን በመጠቀም ተመሳሳይ መጠኖችና ዝምድናዎችን መረዳትና ሃሳባቸዉን እና እዉቀታቸዉን በመጠቀም ተመሳሳይ መጠኖችና ዝምድናዎችን መረዳት</li></ul></td>
<td>5.3 የቁጥሮች ቅደም ተከተል</td>
<td><ul><li>የተለያዩ ቁጥሮችን የያዙ ካርዶችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ በቁጥር መጠናቸዉ ማወዳደር</li><li>መቶኛዎችን የያዙ ቻርቶችን በማዘገጀት ተማሪዎች የጎደሉ ቁጥሮችን እንዲሞሉ መድረግ</li></ul>
<table>
<tr><td>51</td><td>52</td><td></td><td>54</td><td>55</td><td>56</td><td>57</td><td></td><td>59</td><td>60</td></tr>
<tr><td></td><td>62</td><td>63</td><td></td><td>65</td><td>66</td><td>67</td><td>68</td><td>69</td><td></td></tr>
<tr><td>71</td><td>72</td><td>73</td><td>74</td><td></td><td>76</td><td>77</td><td>78</td><td>79</td><td>80</td></tr>
</table>
<ul><li>የተለያዩ ርዝመት ያላቸዉን ዱላዎች በማዘጋጀት እና በመጠቀም ቁጥሮችን ምልክት በማድረግ ማወዳደር</li><li>“አራተኛዉ ወንበር ላይ የተቀመጠዉ ማነዉ የሚል አይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ“</li></ul></td>
<td>ተማሪዎቹ የቁጥር ደረጃን በመጠቀም ቁጥሮችን በትክክል ማወዳደራቸዉን ማረጋገጥ</td>
</tr>
</table>

<table>
<tr><th>ብቃቶች</th><th>ርዕሶች</th><th>የመማር ማስተማር ስልቶች</th><th>ምዘና</th></tr>
<tr>
<td><ul><li>በሙሉ ቁጥር ዉስጥ ምን ያህል አንዶች እና አስሮች እንዳሉ መንገር</li><li>የአንዶችንና የአስሮችን የቤት ዋጋ ለመዘርዘር ሞዴሎችን መጠቀም</li><li>ቁጥሮችን በሙሉ እና በቀሪዉ መቁጠር እና ባለሁለት አሃዞችን ያላቸዉን የቤት ዋጋ መገንዘብ</li></ul></td>
<td>5.4 አንዶችና የአስሮች የቤት ዋጋ</td>
<td><ul><li>ዱላዎችንና ክሮችን በማዘጋጀት እንድላይ በክር በ10 በ10 ማሰር ከዛም “ምን ያህል አንዶች እና አስሮች እንዳሉ መጠየቅ”</li><li>የቤት ዋጋ ጽንሰሃሳብ ለመገንባት የተለያዩ ሞዴል መጠቀም</li><li>የቤት ዋጋቸዉን በመጠቀም ቁጥሮችን ማወዳደር</li><li>የቁጥር ደረጃን የያዙ ካርዶችን መጠቀም ወይም በጥቁር ሰሌዳ ላይ እያንዳንዱን ሆሄየቤትዋጋእንዲጽፉመጠየቅ</li></ul></td>
<td>ስለ አንዶችና አስሮች ተማሪዎች የሚመልሱትን መልሶች ማረጋገጥ .<br><br>ሞዴሎችን በትክክለኛ መንገድ መጠቀማቸዉን በመመልከት ተማሪዎቹ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡ መጠየቅ</td>
</tr>
</table>

# ምእራፍ 6፣እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ( 27 ክፍለጊዜያት)

## የመማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኂላ፣

- ድምራቸዉ ከ100 ያነሱ ባለሁለት ሆሄዎችን መደመር ይችላሉ
- ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ላይ ባለአንድ ሆሄዎች እና ባለሁለት ሆሄዎችን መቀነስ ይችላሉ
- ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መከፋፈልና መደባለቅን በመጠቀም መደመርና መቀነስ ለመፍታት የተለያዩ ሃሳባዊ ስነ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ባለ አንድ አሃዝ ቁጥር ሳይደረድሩ መደመር እና መቀነስ<br>• ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ባለ አንድ አሃዝ ቁጥር ጋር በመደርደር መደመር<br>• ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን ያለአንድ አለኝ መደመር እና መቀነስ<br>• አንድ አለኝን በመጠቀም ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ<br>• እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመርና በመቀነስ የቃላት መልመጃዎችን መፍታት | ምእራፍ 6፣እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ<br>6.1 ከባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ባለመደርደ ርመደመርና መቀነስ<br>6.2 ባለ ሁለት አሃዝ ሙሉ ቁጥሮችን በመደርደር መደመር እና መቀነስ<br>6.3 ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን ያለብድር መደመር እና መቀነስ<br>6.4 ባለ ሁለት አሃዝ ቁጥሮችን በብድር መደመር እና መቀነስ<br>6.5 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በመጠቀም የመደመር እና የመቀነስ የቃላት መልመጃዎችን መስራት | • ባለ አንድ አሃዝ ቁጥርን በባለ ሁለት አሃዝ ቁጥር በተለያዩ ዘዴዎች መደመርና በቁጥር መስመር ላይ ማስቀመጥን መለማመድ<br>• ቁጥሮችን ባለመደርደር መደመርን ማለማመድ ለምሳሌ 37+6=፣ 37=3 አስሮችና 7 አንዶች ቀጥሎ ባለ አንዶችን መደመር 6 እና 7 ፣6+7=13 እናገኛለን 1 አስሮችና 3 አንዶች፣አንድ አስሮችን በ3 ላይ በመጨመር 43 እናገኛለን።<br>• የአስተሳሰባቸዉን አቅም በመጠቀም በመከፋፈልና በመደባለቅ የመደመርና የመቀነስ ፕሮብሌሞችን መፍታት<br>• ወደ ኂላ መቁጠርና በቁጥር መስመር ላይ ከባለ ሁለት ሆሄዎችን ላይ ባለ አንድ አሃዞችን መቀነስን ይለማመዳሉ<br>• አለኝታን በመጠቀም መቀነስን መለማመድ ለምሳሌ 82 — 6 = 82፣ 82 ማለት 8 አስርና 2 አንዶች፣ አንድ አስርን ለአንድ ቤት እንበዳደራለን 2 የነበረዉ 12 አንዶች ይኖሩናል።በመቀጠልም ከ12 ላይ 6 እንቀንሳለን 6 ይቀረናል<br>• ባለ አሃዝ ሆሄ ቁጥሮችን የያዙ ቀላል የመደመር የቃላት መልመጃዎችን መፍታት | • ተማሪዎቹ የመቀነስ ስሌትን በትክክል መጠቀማቸዉን መመልከት<br>• ተማሪዎቹ ያላቸዉን የማስላት ክህሎታቸዉን መመዝገብ<br>• የወረቀት ፈተናዎች |

## ምዕራፍ 7 የተለመዱ ቅርጾች (16 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

- ርዝመትና ወርድ ያላቸዉን ምስሎች በስማቸዉ ይለያሉ፡፡እንደ ግማሽ ክብ፣ዳይመንድ፣ሞላላ፣ባለአምስት ጎን እና ባለስድስት ጎን
- የቅርጾችን ባህሪያት በራሳቸዉ ቋንቋ ይገልጻሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ርዝመትና ወርድ ያላቸዉን ምስሎች በስማቸዉ መለየት፡እንደ ግማሽ ክብ፣ ዳይመንድ፣ሞላላ፣ ባለአምስት ጎን እና ባለስድስት ጎን<br>• አንግልና ጎን በመጠቀም ቅርጾችን መግለጽ<br>• የቅርጾችን ባህሪያት በራሳቸዉ ቋንቋ መግለጽ | ምዕራፍ 7 የተለመዱ ቅርጾች<br>7.1 ርዝመትና ወርድ ያላቸዉን ምስሎች በስማቸዉ መለየት<br>7.2 ርዝመትና ወርድ ያላቸዉን ምስሎች መሳል<br>7.3የጂኦሜትሪ ምስሎችን መለየት | • ግማሽ ክብ፣ዳይመንድ፣ሞላላ፣ባለአምስት ጎን እና ባለስድስት ጎን ሞዴሎችን ማቅረብ<br>• ስለጎኖች እና መለያያዎች መጠየቅ<br>• ተማሪዎች ስለ ግማሽ ክብ፣ዳይመንድ፣ሞላላ፣ባለአምስት ጎን እና ባለስድስት ጎን ስሞች ላይ የአካባቢ መጠሪያቸዉን እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ለተማሪዎች የግማሽ ክብ፣ዳይመንድ፣ሞላላ፣ባለአምስት ጎን እና ባለስድስት ጎን ትክክለኛ መጠሪያ ስሞችን መንገር | •ተማሪዎች ቅርጾችን የለዩበትን መንገድ፣ ምክንያታቸዉን የቃላት ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>•ቅርጾችን የለዩበትን መንገድ ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 8፣ ንድፎች( 16 ክፍለ ጊዜያት)

### የማመር ዉጤቶች ፡- ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

- ተደጋጋሚ ንድችን ይገነዘባሉ፡፡
- ተደጋጋሚ ንድችን ይሰራሉ፡፡

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ከሁለት በላይ ያላቸዉን ንድፎች መገልበጥ<br>• ንድፎችን ማስቀጠል<br>• ተደጋጋሚ ንድፎችን መፍጠር | ምእራፍ 8 ንድፎች<br>8.1 ንድፎችን መገልበጥ<br>8.2 ንድፎችን ማስቀጠል<br>8.3 ንድፎችን መፍጠር | • ጥበብን በመጠቀም ንድፎችን በተደጋጋሚ ስለዉ እንዲወያዩ ማድረግ እና ገልብጠው እንዲሰሩ ማድረግ<br>• ሶስት የንድፍ አባላትን በመስጠት ተማሪዎች ንድፍን እንዲያስቀምጡ ማድረግ<br>• ጥበብን በመጠቀም ህጻናት ንድፊ እንዲሰሩ ማድረግ | • ምልከታ ማካሄድ<br>• ተማሪዎች ንድፎችን ማስቀጠላቸዉንና መፍጠራቸዉን የሚለይ ሙከራ መስጠት |

## ምዕራፍ 9፣ርዝመት፣ መጠነ ቁስ እና ይዘትን መለካት (25 ክፍለጊዜያት)

**የመማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣**

- ባህላዊ የመለኪያ ምድቦችን በመጠቀም ርዝመትን፣ክብደትና ይዘትን ይለካሉ፡፡
- የቁሶችን ርዝመታቸዉ፣ክብደታቸዉንና ይዘታቸዉን መሰረት በማድረግ ያወዳድራሉ፡፡

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| • ርዝመትን በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪያዎች መለካትና በሳ.ሜ እና በሜ መለካት<br>• መጠነ ቁስን በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪያዎች መለካት እና በኪ.ግ እና በግ መለካት<br>• ይዘትን በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪዣዎች ቁና፣ኩባያ እና በሊትርና በሚሊሊትር መለካት<br>• ተመሳሳይ ምድቦችን መደመርና መቀነስ | 9.1 ባህላዊ የኢትዮጵያ መለኪያዎችን በመጠቀም ርዝመትን መለካት<br>9.2 ርዝመቶችን ማወዳደር<br>9.3 ባህላዊ መለኪያዎችን በመጠቀም መጠነ ቁስን መለካት<br>9.4 ክብደትን ማወዳደር<br>9.5 ባህላዊ መለኪያዎችን በመጠቀም ይዘቶችን መለካት<br>9.6 ይዘትን ማወዳደር | • ተማሪዎች የተለያዩ የቁስ ርዝመቶችን ስንዝር፣ እግርና እጅ በመጠቀም እንዲለኩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በአካባቢያቸዉ የሚገኙ ቁሶችን ምሳሌ የዴስክ፣የመጽሀፋቸዉ ርዝመቶች እንዲለኩ ማድረግ<br>• ተማዎች ሜትርና ማስመሪያን በመጠቀም ረጃጅም ርዝመቶችን እንደ የመማሪያ ክፍል ቁመትና የመጫዎቻ ሜዳን እንዲለኩ ማድረገ እና በመጨረሻም የተገኘዉን ርዝመቶች እንዲደምሩ ማድረግ<br>• ጥንድ ቁሶችን በመዘጋጀት ተማሪዎች የቁሶችን ርዘመት እንዲለኩ ማበረታትና የትኛዉ ቁስ ረዥም እና አጭር ነዉ ብለዉ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ሳ.ሜ እና ሜ ያለዉን ማስመሪያ በመጠቀም ያላቸዉን ግንኙነት ያዉቃሉ ምልክቶቻቸዉም ይጠቀማ<br>• ቁሶችን በቤታቸዉ በአካካቢያቸዉ ወይም በሱቅ እንዴት እንደሚለኩ እንዲናገሩ መድረግ<br>• ጥንድ ቁሶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች የቁሶችን መጠነ ቁስ እንዲያወዳድሩ ማነሳሳት<br>• ተማዎችን ባህላዊ የይዘት መለኪያ ምድቦችን ቁና፣ኩባያ፣ትናንሽ መያዣዎችን እና ሊትር በመጠቀም እንዴት እንደሚለኩ ዉይይት እንዲያደረጉ ማድረግ<br>• ተማሪዎች የመያዣዎች ይዘትን አሸዋና ዉሃን በመጠቀም እንዲያወዳድሩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በሊትር የተሰጡ የቃላት ፕሮብሌሞችን መደመርና መቀነስን በመጠቀም መፍታት | • ተማሪዎች የተሰጠ ቁስን በትክክል መለካታቸዉን መመልከት<br>• ተማሪዎች የተለያዩ ቁሶችን በርዝመታቸዉ በመጠነ ቁሳቸዉ እና በይዘታቸዉ በትክክል ማወዳደራቸዉን ማረጋገጥ |

## ምእራፍ 10፣የኢትዮጵያ ገንዘብ (8 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ዉጤቶች፣ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

የኢትዮጵያዉን ሳንቲሞችና የብር ኖቶችን ይገነዘባሉ።
የኢትዮጵያን ብሮችና ሳንቲሞች ያላቸዉን ዝምድና ይረዳሉ።

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የኢትዪጵያን ሳንቲሞች እና ብሮች ይገነዘባሉ<br>• በብርና በሳንቲሞች መካከል ያሉትን ዝምድናዎች ይናገራሉ | 10.1 የኢትዮጵያ ኖቶችና ሳንቲሞች<br>10.2 የሳንቲሞችና የብር ኖቶች ዝምድና<br>10.3 የቃላት መልመጃዎች | • የኢትዮጵያን የተለያዩ ሳንቲሞችን እና የብር ኖቶችን በመሰብሰብ ማስተዋወቅ ለምሳሌ 1 ሳንቲም፣ 5 ሳንቲም፣10 ሳንቲም፣25 ሳንቲም እና 50 ሳንቲም<br>• በአስርሳንቲም እና በ1 ብር መካከል ያለዉን ዝምድና በተመለከተ ዉይይት ማካሄድ<br>• ተማዎች የተለያዩ ሳንቲሞችንና የብር ኖቶችን ለይተዉ እንዲያዉቁ ምቹ ሁኔታ መፍጠር<br>• ተማሪዎች በተለያዩ የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችና መካከል እኩል ዋጋ ያላቸዉን እንዲያሳዩ ማድረግ<br>• ግብብይትን መሰረት ያደረገ የቃላት መልመጃዎችን እንዲፈቱ ማድረግ | • በተማሪዎች የኢትዮጵያን የብር ኖቶችና ሳንቲሞችን በማሳየት የሁለቱን ግንኙነት እንዲናገሩ ማድረግ<br>• የቁጥሮችንና የገንዘብን ግንኙነት በመረዳት የገንዘብ አጠቃቀምን መረዳታቸውን ማረጋገጥ |

## ምእራፍ 11፣የኢትዮጵያ ጊዜ( 8 ክ/ጊዜያት)

### የመማር ዉጤቶች፣ ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ በኋላ፣

- የሳምንቱን ቀናት ስሞችን ይጠራሉ።
- ጊዜን በሰኮንዶች፣ በደቂቃዎች እና በሰአት ይናገራሉ

| ብቃቶች | ርዕሶች | የመማር ማስተማር ስልቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የሳምንቱን ቀናት ስሞችን መጥራት።<br>• ጊዜን በሰኮንዶች፣በደቂቃዎች እና በሰአት መናገር<br>• ባለ 1 ደረጃ መልመጃዎችን ይሰራሉ | 11.1 የኢትዮጵያ ጊዜ አቆጣጠር( 2 ክፍለ ጊዜያት)<br>11.2 የሳምንቱ ቀናት (4 ክፍለ ጊዜያት)<br>11.3 በጊዜ የተሰጡ የቃላት መልመጃዎችን መፍታት (4 ክፍለ ጊዜያት) | • ተማሪዎች በቀን ዉስጥ የሚጠቀሙ የተለያዩ ጊዜያትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ ለምሳሌ ጠዋት፣ከሰአት፣ምሽት እና ማታ<br>• ተማሪዎች በቀን ዉስጥ ባሉ የተለያዩ ጊዜያቶች ጠዋት፣ ከሰአት፣ምሽት እና ማታ ምን እንደሚከናዉኑ መጠየቅ<br>• ለተማሪቹ ቀኑን ይንገሯቸው እና ከቀኑ በፊት እና በኋላ ያሉትን ቀናት ይጠይቋቸው<br>• በአንድ ደረጃ ብቻ የሚመለሱ ጥያቄዎች ይስጧቸው | ተማሪዎች የያዙትን ዝርዝር ተመልከቱ እና እንዴት ጥያቄ እንደሚመልሱ አረጋግጡ |